**በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ**

**ቤተ ክርስቲያን በርን አቡነ ተክለ ሃይማኖት**

**ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት**

**Äthiopische Orthodox Tewahedo**

**Kirche in der Schweiz**

**Bern Heilige Tekle Haimanot Kirche**

=====================================================================

ሐምሌ 10 ቀን 2002 ዓ.ም.
July 17 , 2010

**ለ ስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ሰበካዎች አስተባሰባሪ ኮሚቴ፤**

በቅድሚያ በበርን ሰበካ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የስዊዝ ኮሚቴ ዋና ሥራ የማስተባበርና በሁሉም ሰበካዎች የጋራ ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች የማስፈጸም ኃላፊነት እንዳለው
በ March 28, 2009 በተደረገው የሁሉም ሰበካዎች ጠቅላላ ጉባኤ ገልጸናል። በዚሁ ወቅት የበርን ሰበካን አቋምና ከአስተባባሪው ኮሚቴ ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት በደንባችን ረቂቅ ላይ የተካተተውን አስረድተናል። በዕለቱ ለአስተባባሪ ኮሚቴ አዲስ ውክልና ለመስጠት በተደረገው ምርጫ 5 ቱም አባላት በአቶ ሚስጢረ ኃይለ ሥላሴ ጥቆማ ብቻ ምንም ድምጽ ሳይሰጥ ሲመረጡ፣ የበርን ሰበካን ያገለለ እንደነበርና አሰራሩም ትክክል አይደለም በማለት የሁሉም ሰበካዎች ውክልና ያስፈልጋል ብለን አንድ ሰው በእኛ በኩል እንድንወክል ጠይቀን ወ/ሪት ዕምነት ታደሰን መወከላችን ይታወቃል።

እስኪ ለተመልካች ፍርድ እንዲሆን ስዊዝ ኮሚቴ ውስጥ ያሉትን አባላት በየሰበካቸው እና በኮሚቴዉ ውስጥ ያላቸውን ኃላፊነት እናስተዋዉቃችሁ።
ዶ/ር መርዕድ ታየ . . . . . የሎዛን ሰበካ ሊቀ መንበርና የስዊዝ ኮሚቴ ሰብሳቢ
አቶ ሱራፌል ኪዳኔ. . . . . የሎዛን ሰበካ ም/ሊቀ መንበር እና ስዊዝ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ
አተ ጌታቸው ግርማ . . . . .የዙሪክ ሰበካ ገንዘብ ያዥ እና የስዊዝ ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ
አቶ ተስፋ ወ/ሥላሴ. . . . ከአራው ሰንበት ት/ቤት የስዊዝ ኮሚቴ ጸሐፊ
ወ/ሪት ዕምነት ታደሰ. . . . የበርን ሰበካ ኮሚቴና የስዊዝ ኮሚቴ አባል ናቸው ።

የእነዚህን ሰዎች ማንነትና ዓላማቸውን ለሚያዉቃቸው ብንተወው ይሻላል። ዋናው ነገር ግን የሎዛን ወይም ዙሪክ ሰበካ በስዊዝ ኮሚቴ ውስጥ ባላቸው ቦታ ለበርን ሰበካና ለሰንበት ትምህርት ቤቶች የበላይ ውሳኔ ሰጪ መሆናቸውን ያሳየናል። ይህ ደግሞ በስዊዝ ሰበካዎች መካከል የሚኖረውን እኩልነትና ነጻነት የሚጻረር ነው። ያለንበት ሀገር የሰጠንን መብትና ነጻነት የሚገፍም ነው ።

አዲሱ የበርን ሰበካ መተዳደሪያ ደንብ በምዕመናን ከጸደቀ ከ August 15 , 2009 ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ነው። የስዊዝ ኮሚቴም ደንባችንን እንዲያዉቁት August 31, 2009 ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ተሰጥቷችሁ እና እስከ አሁን ምንም ዓይነት ይፋ የሆነ አስተያየት ሳትሰጡበት በደንባችን መሠረት በጋራ መንፈሳዊ አገልግሎት ስናካሂድበት ይኸው አንድ ዓመት ሊሆነው ነው። ከዚህ ውጭ የስዊዝ ኮሚቴ ከአስተባባሪነት አልፎ አዲስ ስያሜና መብት ማን እንደሰጠው በእኛ በኩል የሚታወቅ ነገር የለም። ሆኖም በእናንተ አንዴ አቢይ ኮሚቴ፤ አንዴ ማዕከላዊ ኮሚቴ፤ አንዴ አጠቃላይ የስዊዝ ኮሚቴ ብትሉትም ደንባችንን እስከተቀበላችሁ ድረስ የስዊዝ ኮሚቴ የተለያየ ስያሜ መያዙ ችግር አያመጣብንም ብለን ነበር። አሁን ግን የበርን ሰበካን ደንብ የጣሰ እና ጭራሽ ምዕመናንን በዘር የሚከፋፍል፣ መንፈሳዊ እና ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያፈራርስ መሰሪ ሥራ ስትፈጽሙ በማየታችን ማንነታችሁን እና መብታችሁ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ እንድናሳዉቃችሁ እንገደዳለን።

በተለይም የበርን ሰበካን ውሳኔና ደንብ አንቀበልም ኮሚቴውንም በጊዚያዊ ኮሚቴ በሞግዚትነት እንመራለን ማለታችሁ በስዊዝ ሀገር እናትና አባት ልጃቸውን፣ሚስት ባሏን ባልም ሚስቱን እንደፈለገ ማዘዝ በማይችልበት ህግ እየተዳደራችሁ በበርን ሰበካ ምዕመናን ላይ ግን ይህን ማሰባችሁ የእናንተን ማንነት የበለጠ ይገልጸል። እናንተንም እነዚህ ሰዎች በእውነት የሚሰሩትን ያዉቃሉ? ወይስ አያዉቁምና ይቅር በላቸው ብለን በጸሎት እናስባቸው ይሆን እንድንል አድርጎናል።

የሰራችሁትን መንፈሳዊ ያልሆነ ሥራ ማለትም ምዕመናኑን በዘር የሚያደራጅ ከፋፋይና ህገ ወጥ መልዕክታችሁን አንድ በአንድ እያየን እንደሚከተለው መልስ እንሰጥበታለን።

**1. " ስብሰባው በጸሎት ተከፍቶ ለመረጃ እንዲረዳ በቪዲዮ ስብሰባው እንዲቀረጽ ፈቃድ ተጠይቆ በሙሉ ድምጽ ጸደቀ..." ይላል።**

ቪዲዮው ለምን አልተላከልንም? መረጃነቱስ ለምንና ለማን የተዘጋጀ ነው? መንፈሳዊ የሆነ ያውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስብሰባን በቪዲዮ መቅረጽ ለምን ፈቃድ አስፈለገው? መልሱን ከእናንተው ብንሰማ ደስ ይለናል።

**2. በስዊዘርላንድ አቢይ ኮሚቴ የተነበበው ጽሑፍስ ለምን በሚስጢር ተያዘ.... ? ሃይማኖት ወይስ የፖለቲካ አሠራር ...?**

**3. ስዊዘርላንድ የሚገኙ ሰበካዎችና ሰንበት ትምህርት ቤቶች በሙሉ የሚተዳደሩበት በሶስቱም ካህናት እንደገና ተዘጋጅቶ የቀረበው ደንብ ተነበበ.... " ተብሏል።**

ደንቡ ለምን በስብሰባ ብቻ ተነበበ?ለምን ይፋ አላወጣችሁትም ? ለሌላው የስዊዝ ምዕመናን ሳይነበብ ለበርን ምዕመናን ብቻ ለምን ተነበበ? ይህን ደንብ በስዊዝ ሁሉም ምዕመናን ሳይመክርበት እና ሳያውቀው ሁሉም የበርን ሰበካ ምዕመናን ባልተገኙበት አጸድቆ ለሁሉም መመሪያ እንዲሆን ለምን ተወሰነ?
በስዊዝ ያለው ቤተ ክርስቲያን ገለልተኛ ነው እያላችሁ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ የምንከተለውና መመሪያ የምንቀበለው ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ ነው ትሉናላችሁ። እስኪ እግዚአብሔር ያሳያችሁ እና የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ ከተከተላችሁ ገለልተኛነታችሁ ምኑ ላይ ነው? ፍርዱን ለአንባቢው እንተወው። እዚህ ላይ በስዊዝ የሚገኙ ሁሉም ምዕመናን ልብ ብለው ይመርምሩት። ድብቅ ሥራ ማለት ይኸ ይመስለናል።

**4. "የበርነ ሰበካን ችግር በተመለከተ በበርን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰበካ ጉባኤ ስም እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ድብቅና ከምዕመናኑ ሃሳብና ፍላጎት ውጭ ተለይቶ የተወሰኑ ግለሰቦች ፍላጎት ያንጸባረቀ ነው ..."ተብሏል።**

ድብቅ እንቅስቃሴ ነው ሲባል መደበቁን እንዴት አወቃችሁት? ድብቅ ዓላማውስ ለምን አልተገለጸም? በእኛ በኩል ግን ግልጽና የሁሉም ምዕመናን ተሳትፎ ያካተተ ለሁሉም ምዕመናን አንድነት የሚጠቅም ደንብ በይፋ ማጽደቃችንን ነው የምናውቀው። በቤተ ክርስቲያንም ከጸሎት፣ ከወንጌል ትምህርት፣ ከቅዳሴ እና ክብረ በዓላትን በንግሥ ከማክበር ውጭ የተካሄደ ድብቅ ዓላማ እንደሌለን በዓይን የታየ፣ በጆሮ የተሰማ፣ በአፍንጫ የተሸተተ፣በምላስ የተቀመሰ መንፈሳዊ አገልግሎት መሆኑን ክህጻን እስከ አዋቂ ይመሰክርልናል። በተለይም ደግሞ አዲስ ካህን መጋቢ ሥርዓት ቀሲስ አበባው አዳነ ወደ ሰበካችን ሲመጡ በባህላችን እና ዕምነታችን መሠረት መልካም እረኛ አገኘን ብለን በመደሰት በእንግድነት አክብረን ተቀብለን ከየትና እንዴት እንደመጡ እንኳ ሳናዉቅ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ደንባችንን አይተው እንዲያስተካክሉት እና ካመኑበት በኋላ በርሳቸው መንፈሳዊ ማብራሪያና ገለጻ ማጸደቃችን፣ በስዊዝ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለካህን ተሰጥቶ የማያውቀዉን የሰበካችn አስተዳዳሪ እና የሰበካ ጉባኤ ሰብሳቢ እንዲሆኑ በኮሚቴው እና ምዕመናኑ መልካም ፈቃድ ካለምርጫ ማስደረጋችን እና የመሳሰሉት ይሆን ድብቅ ዓላማ አላቸው የሚያስብለን ? ? ? አሁን እየተወነጀለ ያለው የበርን ሰበካ ኮሚቴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታላቅ ዕድገትን ያሳየው የበርን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በወጣትና ህጻናት መዘምራን ተደራጅቶ ላሳየው መንፈሳዊ ዕድገት በየጉባኤው በአባቶች ሲወደስ እንደነበር የስዊዝ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምዕመናን በሙሉ የሚያረጋግጡት ሀቅ ነው። ዛሬ ደግሞ ይህንን እውነታ ድብቅ ዓላማ ነው የሚሉን ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶላቸው በሰገነት ላይ ወጥተው መንፈስ ቅዱስ የሚያዛቸውን ሳይሆን የግል ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ካለምንም ህግ ባይ ሲሰብኩን

ከነበሩት ካህናትና በየሰበካቸው አጼ ነን ግዛታችንም በሁሉም ስዊዝ ነው ..."የሚሉትን ከዘመኑ ጋር ሳይሆን በራሳቸው የህልም ዘመን ያሉትን እንደሆነ የዚህ ስብሰባ አቀነባባሪዎች ታውቁታላችሁ።

5. በማያያዝ ደግሞ **"ቤተክርስቲያኗን የግላቸው እንደሆነች እና በራሳቸው መንገድ ሊመሯት በመፈለጋቸው ምክንያት ከፍተኛ ልዩነት መፍጠራቸው ታዉቋል..."** ተብሏል።

እዚህ ላይ የእምዬን ወደ አብዬ የሚባለውን አባባል ያስታዉሰናል። በየራሳቸው ሰበካ ውስጥ ያለውን ቤተ ክርስቲያን ማን ለዘመናት እንደ ግል ንብረት  እንደያዘው በስዊዝ የሚኖረው ድፍን ኢትዮጵያዊ የሚያዉቀዉ ነው። የቤተ ክርስቲያኑን ባለ ሀብቶች ፈቃድ የማይፈጽም ስንቱ ንጹህ ምዕመናን ቤተ ክርስቲያንን እንደተወ ልባችሁ ያውቀዋል።የበርን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያንን በዘር በማሰባሰብ እንዲሁም በወዳጆቻችሁ እና በጥቅም በያዛችኋቸው ካህን እና ሰዎች አማካይነት ሰላምና ፍቅር የነበረውን ምዕመናን የመበታተን ሴራ የተደረገው በማን ነው? በ July 10,2010 የተደረገው ስብሰባም የዚህ ሤራ ማረጋገጫ ነው።

የበርን ሰበካ ለበርን ሰፊ ምዕመናን ነጻ መገልገያ እንደሆነ በደንባችን የተደነገገውን እና ከምሥረታ እስከ አሁን ድረስ የተሠራው ተግባራዊ ሥራ  መንፈሳዊ ለሆንና በዕምነት ለሚገኘው ምዕመናን መንገር ለቀባሪው አረዱት ነው። እንግዲህ አሉባልታውን ያወሩት ሰዎች ለምን በበርን ምዕመናን ፊት ቀርበው ወይም ማስረጃቸውን በጽሑፍ አቅርበው አላጋለጡም። ማንን ፈሩ? ካህኑ በመስቀል ጠረጴዛ  በመደብደብና ምዕመኑ በስድብና በዛቻ ሁከት ከመፍጥር ይልቅ ጥፋቱን በማስረጃ እያቀረቡ አጥፊዎች የኮሚቴ አባላት ላይ በበርን ምዕመናን ውሳኔ እንዲሰጥበት ለምነ አላደረጉም? መራጭና ተመራጭ እያለ ከሰበካችን ውጭ ያሉትን እርዱን ድረሱልን ማለት ለምን አስፈለገ...? ፍርዱን ለታዛቢ !!!

6. **"አብዛኛዎቹ የበርን ምዕመናን በዚህ ህገ ወጥ ስብሰባ እንደተገኙ ተገልጾ ስብሰባውን የተቃወሙት ውስን የኮሚቴ አባላት ብቻ ባይገኙም ፍላጎታቸውን በቅርብ በተረዱ  ምዕመናን አማካኝነት ሀሳባቸው ለተሰብሳቢው እንዲደርስ  ሆኗል ..."** ተብሏል።

እዚህ ላይ የስለላ ስራም እንደተካሄደ ያስረዳል። እኛ ደግሞ ሀሳባችንን በሰፊው አትተን አስተላልፈን ነበር። ምነው በቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ላይ ተወያይታችሁ የማስተባበያ መልስ አልሰጣችሁበትም። ሁላችሁም በእድሜ ትልልቆች ናችሁ፤  በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈውንስ  መረዳት አቃታችሁ ይሆን?

7. **"በበርን ሰበካ ስም ጁላይ 3 ቀን 2010  አስቸኳይ ስብሰባ ተደርጎ ተላለፈ የተባለው ውሳኔ ምልዓተ ጉባኤ ሳይኝን የተከናወነ መሆኑ በማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል።"** የሚለው

ማስረጃውን እኮ እኛ ነው የሰጠናችሁ። ድብቅ ካሜራ ነበር እንዴ...? ወይስ  ለመረጃ ሰብሳቢነት የተላኩት  ወ/ሪት ዕምነት ታደሰ መረጃ አቀረቡላችሁ? እኛም ሆነ ሌላው ቢያውቀው ጥሩ ነበር። ስለነበረው አስቸኳይ ስብሰባ እና ምልዓተ ጉባኤውን በሚመለከት በቂ ማብራሪያ ሰጥተንበታልና እንደገና በ July 3,2010 ያስተላለፍነውን ጽሑፍ ተመልከቱት።

8. **"ይህንኑ ውሳኔ የስዊዝ ኮሚቴም ሆነ የበርን ምዕመናን በምንም መመዘኛ ሊቀበሉት እንደማይችሉ በአጽንኦት ገልጸዋል።"** ተብሏል።

በማያያዝ ደግሞ **"በዚሁ ስብሰባ በበርን ምዕመናን የተወሰነውን ውሳኔ የስዊዝ ኮሚቴ ተቀብሎ በበርን ሰበካ ጉባኤ ስም ለበርን አቡነ ተክል ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ይሆናል ተብሎ የተነደፈውን መተዳደሪያ ደንብ እንደማይቀበለው ይፋ አድርጓል።"** ይላል።
ከአጻጻፉ በዕለቱ ተገኙ የተባሉትን የበርነ ሰዎችን የማታለል አካሄድ እንዳለ ይጠቁማል። ምክንያቱም በ ጁላይ 3 ስለተላለፈው ውሳኔ ተናግራችሁ መተዳደሪያ ደንቡን መሻራችሁን ገልጻችኋል። ወይም የአጻጻፍ ስህተት ከሆነ አርሙት። ለማንኛውም የጁላይ 3 ቀን 2010 የበርን ሰበካ ኮሚቴ ውሳኔን እና ደንቡን የመሻር መብት ያለው የበርነ ምዕመናን እንጂ የሌላው ሰበካ አጼዎች ወይም የእነርሱ  ዓላማ አስፈጻሚ  ሰዎች ሊሆኑ አይችሉም።

10. **አስገራሚው ደግሞ ሁሉንም ውሳኔዎች በስዊዝ ኮሚቴ አባላት ሰብሰባቢነት ካስፈጸሙና ውስንና ድብቅ ዓላማ አላቸው የተባሉትን የበርን ኮሚቴ አባላት ካወገዙ በኋላ "በበርን በኩል ለሚታየው አለመግባባት የበርነ ምዕመናን ከሃይማኖት አባቶች ጋር ሆነው በግልጽነት እንዲወያዩ በማሰብ አጠቃላይ ኮሚቴው ከስብሰባው አዳራሽ ወጥቷል ።** ተብሏል።  ምን ቀርቶ ይሆን ስንል  ወረድ ብሎ " **የበርን ምዕመናን ከአባቶች ጋር በመሆን የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት ይመቻቸው ዘንድ በስፋት ከተወያዩ በኋላ በዕለቱ በስብሰባው ከተገኙት መሀከል ቀድሞ በሰበካ ኮሚቴነት ካገለገሉት ውስጥ ወ/ሪት ዕምነት ታደሰን ጨምሮ በድምሩ አምስት የጊዚያዊ ኮሚቴ አባላትን መርጧል ። የሥራ ድርሻቸውም ተገልጿል።**"ይላል።

ከስብሰባው ፍጻሜ ጀምሮ ተመረጡ የተባሉት "አስታራቂ ሽማግሌዎች ሆነን በፈቃዳችን ተወክለናል ከሁሉም ወገን ነጻ ነን..." እያሉ ሰሞኑን በተናጥል ሲያነጋግሩን ከነበረው አባባላቸው ጋር ይጋጫል። ወይም የስዊዝ ኮሚቴ ውሳኔውን በድርጅታዊ አሰራር ለማስፈጸም ያካሄደውን ድራማ ያጋልጣል።

ለማንኛውም ተመረጡ የተባሉት ከወ/ሮ ኤልሳ በላይ በስተቀር የበርን አቡነ ተክለ ሃይማኖት መሥራችና ነባር አበላት ስለሆኑ በራሳቸው በበርን ሰበካ ውስጥ ያለውን ተግባራዊ ሥራ የሚመሰክሩና ጥፋተኛውን የሚያውቁ ወይም ተፈጠረ ለተባለውም ችግር አካል ስለሆኑ በስዊዝ ሰበካ ኮሚቴ መሾማቸው አስገርሞናል። ሹመት ያዳብር ከማለት ሌላ ምን ይባላል። ለምን ወንዶች በዚህ ሹመት ውስጥ እንዳልተካተቱ ግልጽ አልሆነልንም። ወይስ በስብሰባው የተገኙት ሴቶች ብቻ ነበሩ?  በዚህ አጋጣሚ በየዋህነት በማያዉቁት ጨዋታ እንዲገቡ የተደረጉ ካሉ ከወዲሁ ስህተቱን ቢያርሙት በዕምነታቸውም ሆነ በማህበራዊ ኑሮአቸው ላይ ችግር ላለመፍጠር ይረዳቸዋል እንላለን።

11. **በመጨረሻ ጊዚያዊ አስተባባሪ ኮሚቴው በቀጥታ ከስዊዝ ኮሚቴ ጋር ግንኙነት ያደርጋል ይላል።**

ይህ ማለት ደግሞ ከእንግዲህ የበርን ምዕመናን በስዊዝ ኮሚቴ ሹሞች እንጂ በራሱ መስተዳደር በሚመርጣቸው ኮሚቴዎች እንደማይመራ ማስባቸሁን ያረጋግጣል። ይህ ደግሞ ነግ በእኔ ነውና በስዊዝ  ያላችሁት ምዕመናን እንድታስቡበት እናስታውሳችሁ። ከሁሉም በላይ የበርን ምዕመናን የቅዱስ እግዚአብሄርን መልካም ፈቃድ ሆነ የጻድቁ አባታችን ተክለ ሃይማኖትን ተራዳይነት ሲጠይቁ እና ሲማጸኑ ከነበሩት ውስጥ ያሰቡት ሲሳከላቸው በማህበር ጸሎት፣ በቅዳሴ፣ በወንጌል ትምህርት እና በደስታም አብረው ለ 6 ዓመታት ያሳለፉት ያን መልካም ጊዜ ረስተውት የመከፋፈልና የመለያየት ሴራ ተዋንያኖች ሲሆኑ ተክልዬስ ምን ይሏቸው ይሆን?
የበርን ሰበካ ምዕመናን የወከላቸው እና በፈቃዳቸው ኃላፊነትን በመወጣት እስከ አሁን የሠሩት የኮሚቴው አባላት አሁንም የበርን ምዕመናንን ወክለው እስከ August 7 ቀን 2010 ማለትም አስቸኳይ የምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ ሥራቸው ይቀጥላል።

የጁላይ 10 ቀን 2010 ስብሰባም  የስዊዝ ኮሚቴ በዘርና በጥቅም እንዲሁም አንዳንድ ነገሩ ያልገባቸውም ጥቂት ምዕመናን በየቤታቸው ስልክ በመደወል እና በማባበል „ ያሰባሰባቸውን ጥቂት ምዕመናን ውሳኔ  የበርን ሰበካ ኮሚቴ ውድቅ አድርጎታል። ሁሉም ነገር  በሚቀጥለው የምዕመናን ጉባኤ ላይ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበታል።

በተላለፈልን መልዕክት ይህን ካልን ወደፊት የሚወጡና አሁንም በሚስጢር የተያዘው ሁሉ ይፋ ሲሆን መልስ እንሰጥበታለን።

**የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ፍቅር ከሁላችንም ጋር ይሁን!!!!**

**በስዊዘርላንድ የበርን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ኮሚቴ**

---

አባሪ:-  የስዊዝ ኮሚቴ ጁላይ 10, 2010 ሕገ ወጥ ስብሰባ እና መልዕክት ( 2 ገጽ )
ግልባጭ ፦
ለ ካህናት
ለ ስዊዝ ሁሉም ምዕመናን
ለ Petruskirche und Kirchgemeindehaus , Brunnadernstr. 40, 3006 Bern
ለ Kirchgemeinde Evangelisch-reformierte Gesamtkirchgemeinde Bern Nydegg
Gemeindehaus Burgfeld, Burgdorfholzstrasse 35, 3006 Bern, Schweiz